የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
ETHIOPIAN PEOPLE PATRIOTIC FRONT

EPPF

# ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የተሰጠ መግለጫ

ሰኔ 22/ 2010

## ሕዝብን በመግደልና ደም በማፍሰስ ስልጣንን ከሕዝብ መንጠቅ ዘበት ነው!!

በኤርትራ ለሚገኘው ታጣቂ ሰራዊት ወደ ሃገሩ ኢትዮጵያ በመመለስ ሰላማዊ ትግል እንዲያደርግ ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ አህመድ እና አዲሱ ካቢኒያቸው የለውጡ ሃዋሪያ በመሆን ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያሳዩትን ለውጥ እጅግ በጣም ከአክብሮት ጋር ልናመሰግን እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ለበርካታ አመታት ለዲሞክራሲ፣ፍትህና እኩልነት ለሁሉም ዜጋ ያለ ዘር መድሎ እንዲከበር የበኩሉን አስተዋፅጾ ሲያደርግ እንደነበር እርሶዎም መንግስትም የሚያውቀው ጉዳይ ነው።

ይህ ስንታገልለት የነበረው የመብት ጥያቄና ፍትህ በአሁን ሰዓት መስመር ይዞ በማየታችን ከልብ የመነጨ ደስታችንን እያቀረብን ድርጅታችን የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የትጥቅ ትግሉን አቁሞ የመልካም አስተዳደርን በተገቢው መንገድ መጓዝ በመደገፍና በመሳተፍ ለለውጡ ድጋፍ ለመስጠት በጋራ የተስማማ መሆኑን ስናበስር ደስታችን ወደር የለውም። በቅርቡም የተደረገለትን ጥሪ ተከትሎ ወደ ሃገር ወስጥ በመግባት ድርሻውን እንደሚወጣ ጽኑ እምነታችን ነው።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር

የሕዝባችን ፍላጎት በሃገራችን ውስጥ በየትኛውም ቦታ ዜጎች ያለስጋት ሰርተውና ንብረት አፍርተው በሰላም መኖር ነው። ሰላም የሚጀምረው ደግሞ ሁሉም ህዝቦች በነጻነት ተፈቃቅሮና ተከባብሮ ያለስጋት በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል መኖር ሲችል ባቻ ነው፣ በዚህ ረገድ በሁላችንም በኩል ብዙ

Email:- eppf.public.relation@gmail.com , phone Number +32493499619 Belgium
+2917563020 Asmara
+49911209433 German
+12096883452 USA

ክክመስራት የሚጠበቅብን ቢሆንም የሃገራዊ አንድነትን መስበኩና ፍቅርና ሰላምን ማዜሙ ፣ማስተማሩ እርሶ እንደሚሉት `` መደመሩ`` አንዱ እና ዋነኛው መንገድ ነው። በሌላ በኩል በጎረቤት ሃገራት ያለማንም ጣልቃ ገብነት  ከኤርትራ ጋር የተደረገው የሁለቱ ሃገሮች የሰላም ስምምነት በእጅጉ ሁላችንን የሚያኮራ ሆኖ አግኝተነዋል።

ይሁንና  በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ በተደረገው የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ አህመድንና ካቢኔው ላሳየው የሕዝባዊ ጥያቄ መላሽ  ለምስጋና በወጣው የድጋፍ ሰልፈኛ ላይ ሆን ተብሎ በጸረ አንድነት ሃይሎች የተፈጸመውን ድርጊት በእጅጉ እንቃወማለን።

ይህንን ሕዝባዊ ለውጥ ለመቀልበስ ሌት ተቀን ያለ እረፍት ለግል ቋሚ ጥቅማቸው የሚሯሯጡ ቡድኖች ሊጋለጡ እና በፈጸሙት እኩይ ተግባር በህግ መጠየቅ አለባቸው ብለን እናምናለን፣ ህዝቡም ድርጊቱን የፈጸሙ ተላላኪዎችንና የጉዳዩ አስፈጻሚዎችን ማጋለጥ ይጠበቅበታል።

እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር  በቀጣይ በሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለውን ለውጥ እናበረታታለን እንደግፋለን፣ሃገራችን ኢትዮጵያ የተያያዘችውን የሰላም፣የዲሞክራሲ፣የፍትህ ለውጥ ጎዳና በእጅጉ እንደግፋለን ለተፈጻሚነቱም በአብሮነት በሰላማዊ መንገድ እንሳተፋለን ።

ጸረ አንድነት ሃይላት በተባበረው አንድነታችን ይጋለጣሉ !

EPPF

አንድነት ኃይል ነው

Email:- eppf.public.relation@gmail.com , phone Number +32493499619 Belgium
+2917563020  Asmara
+49911209433 German
+12096883452  USA